# የ COVID-19 ህክምና

## ለከባድ የኮቪድ ህመም ተጋላጭ ነዎት?



- በጠና የመታመም ዕድላቸው ከፍተኛ የሆኑ ሰዎችን ለመርዳት ህክምና ሊኖር ይችላል።

Public Health
Seattle & King County

ASPR.HHS.GOV/TESTTOTREAT

# የመመርመር ለመታከም ፕሮግራም

መመርመር ለመታከም /Test to Treat/ ሰዎች ተመርምረው COVID-19 ከተገኘባቸው በአፋጣኝ የነፃ ህክምና እንዲያገኙ የሚረዳ አዲስ ፕሮግራም ነው::




· የኢንሹራንስ ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታ ምንም ይሁን ምን የህክምናው ወጪ በነጻ ነው::

Public Health
Seattle & King County

ASPR.HHS.GOV/TESTTOTREAT

# የብቃት መመዘኛ

በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት ለህክምና ብቁ ከሆኑ የጤና እንክብካቤ የሚሰጥዎት ድርጅት ይነግርዎታል::

- ✔ ለከባድ የCOVID-19 አደጋ የመጋለጥ ደረጃዎ
- ✔ አሁን እየወሰዷቸው ያሉት መድሃኒቶች
- ✔ ሌሎች ህክምናዎችን የማግኘት ሁኔታ
- ✔ እድሜ (የግድ 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ ቢያንስ 88 ፓዎንድ ወይም 40 ኪ.ግ መመዘን ያስፈልጋል)::

# ህክምናውን የማገኘው እንዴት ነው?

- በመጀመሪያ የጤና አገልግሎት የሚሰጥዎትን ድርጅት ያነጋግሩ:: አገልግሎት ሰጪ ድርጅትዎ ከማናቸውም ጸረቫይረስ ሊኖር ከሚችልበት ቦታ ሊያገኟቸው የሚችሉትን የመድሃኒት ማዘዣ ሊሰጥዎት ይችላል::

- የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ከሌለዎት በአከባቢዎ የሚገኘውን ክሊኒክ ለመፈለግ መመርመር ለመታከም የት እንደሚገኝ የሚያሳይ /Test to Treat locator/ (aspr.hhs.gov/TestToTreat) ን ይጠቀሙ ወይም በእንግሊዝኛ: ስፓኒሽ: እና ከ150 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች እርዳታ ለማግኘት በ1-800-232-0233 (TTY 888-720-7489) ይደውሉ::

- እቤት ከተደረገው የ(antigen) ምርመራ ወይም ከምርመራ ማዕከል ያገኙትን የምርመራ ውጤት ለመመርመር መታከም በአድራሻው /Test to Treat location/ ይስጡ::

ጥ

## ምን ዓይነት መድሃኒቶች በመመርመር ለመታከም ፕሮግራም/Test to Treat program/ በኩል ይገኛሉ?

መ

የመመርመር ለመታከም ፕሮግራም /Test to Treat program/ ሁለት በአፍ የሚወሰዱ ጸረቫይረስ ክኒኖችን ያካትታል:: – Pfizer’s Paxlovid (Ritonovir-boosted Nirmatrelvir) እና Merck’s Lagevrio (Molnupiravir). እነዚህ መድሃኒቶች ምልክቱ እንደታየ ወዲያውኑ ቢወሰዱ ከባድ የሆነ ህመምንና ሆስፒታል መግባትን ሊከላከሉ ይችላሉ:: መድሃኒቱ የCOVID-19 ምልክቶች እንደጀመሩ በ5 ቀናት ውስጥ መወሰድ ይኖርበታል::

ጥ

## ጥ. በአፍ የሚወሰድ ጸረቫይረስ መድሃኒት የሚሰራው እንዴት ነው?

መ. በአፍ የሚወሰድ የጸረቫይረስ ህክምና ለ COVID-19 መንስኤ የሆነው ቫይረስ በሰውነትዎ ውስጥ እንዳይባዛ በማስቆም: በሰውነትዎ ውስጥ ያለውን ቫይረስ በማሳነስ ወይም በሽታ የመከላከል አቅምዎትን በመደገፍ ሰውነትዎ COVID-19 ን እንዲዋጋ ይረዳል::

መ

Public Health
Seattle & King County

ASPR.HHS.GOV/TESTTOTREAT

ጥ

## በአሁኑ ሰዓት ምን ምን ሌሎች የኮቪድ መድሃኒቶች ይኖራሉ?

በመመርመር ለመታከም ፕሮግራም /Test to Treat program/ በኩል የማይሰጥ ቢሆንም በሽታን የመከላከል አቅማቸው አነስተኛ የሆኑ በሽተኞች ኮቪድን ለመከላከል እንዲረዳቸው Evusheld የተባለውን መድሃኒት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ::

መ

ለEvusheld ብቁ መሆንዎን ለማረጋገጥ የጤና አገልግሎት የሚሰጥዎትን ድርጅት ይጠይቁ ወይም የበርድስ አይ ሜዲካል /the Birds Eye Medical/ ድህረ ገጽን ይጎብኙ:: birdseyemedical.com/evusheld_treatments

# የበለጠ ለማወቅ

ስለመመርመር ለመታከም ፕሮግራም (Test to Treat program) ወይም በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የመርሐግብር አድራሻ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወደ **aspr.hhs.gov/TestToTreat ድህረ ገጽ ይሂዱ::**



Public Health
Seattle & King County